በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
ETHIOPIAN BIODIVERSITY INSTITUTE (EBI)

ቁጥር፡ ኢብኢ/36/820/2014
Ref. No.
ቀን፡ 19 መስከረም 2014
Date

ለተመራማሪዎች የደረጃ ዕድት ኮሚቴ

ኢ.ብሀኢ.

ጉዳዩ፡- <u>በጥቅምት 2013 የተሻሻለዉን የተመራማሪዎች የእድገት መመሪያ ይመለከታል፤</u>

በኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት በቀን 17/12/2013 ዓ. ም ለዋና ዳሬክተር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብዳቤ በ2008 ዓ.ም ፀድቆ በስራ ላይ የነበረዉ የተመራማሪዎችን የደረጃ እድገት መመሪያ ማሻሻያ ተደርጎበት ከጥቅምት 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ቢሆንም በመመሪያዉ ውስጥ ግልፅ ያልሆነና ተጨማሪ ማብራሪያ የሚፈልገውን ክፍል እንደሚገኝ ኮሚቴው በዝርዝር አሳውቋል። በመሆኑም የኮሚቴውን ማሻሻያ ሃሳቦች መነሻ በማድረግ የሚከተሉት ነጥቦች የመመሪያው አካል እንዲሆኑ ተወስኗል።

ሀ. ጊዜው ሳይደርስ የሚሰጥ የደረጃ እድገትን በተመለከተ

1. ጥቅምት 2013 በተደረገው ማሻሻያ ገፅ 9 ንኡስ አንቀጽ 3.4. ጊዜዉ ሳይደርስ የሚሰጥ የደረጃ ዕድገት (Accelerated promotion) በሚለዉ ስር በቁጥር 3.4.3. ከሕትመቶች መካከል ቢያንስ 70% ላይ የመጀመሪያ ጸሀፊ ሆኖ ሲገኝ የሚለው ቀርቶ ከህትመቶቹ ውስጥ ቢያንስ ሁለቱ ላይ የመጀመሪያ ጸሀፊ ሆኖ ሲገኝ በሚል ተተክቷል።
2. ለተባባሪ ተመራማሪ የሚቀርብ የደረጃ ዕድገት ጥያቄ ከተባባሪ ተመራማሪ በፊት ያሉ ደረጃዎች (ጀማሪ ተመራማሪ፣ ረዳት ተመራማሪ I እና II) ህትመት የማይጠይቁ መሆናቸውን ተከትሎ ለመደበኛ የዕድገት ጥያቄ አመልካቹ በነዚህ ደረጃዎች ላይ እያለ ያሳተማቸው ጹሑፎች በሙሉ ለተባባሪ ተመራማሪ ደረጃ ጥያቄ ሲያቀርብ ጥቅም ላይ እየዋሉ ይገኛሉ። ነገር ግን ጊዜው ሳይደርስ የሚሰጥ የደረጃ ዕድገት (Accelerated promotion) ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ዓላማው ተመራማሪው በያዘው መደብ ላይ ሆኖ በአጭር ጊዜ ላከናወነው ውጤታማ ሥራ የሚሰጥ የደረጃ ዕድገት ከመሆኑ አንጻር ረዳት ተመራማሪ II ሆኖ ያሳተማቸው ጹሁፎች ብቻ ለእድገት

ስልክ 011-6-612244
Tel 011-6-512023
011-6-615607
011-6-616643
ፋክስ 011-6-613722
Fax 011-6-612542
E-mail: info@ibc.gov.et
ፖ.ሳ.ቁ. 30726
P.O.Box
Web site: www.ibc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia
መልሱን በሚጽፉልን ጊዜ እባክዎ የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱልን
Please quote our Ref. No. when replying

እንደማሟያ እንዲሆኑ። በጀማሪ ተመራማሪና ረዳት ተመራማሪ I የታተሙ ጽሑፎች መደበኛውን የእድገት ሂደት ተከትሎ ለሚቀርብ የደረጃ እድገት ጥያቄ እንደማሟያ ጥቅም ላይ እንዲውል በሚል ተስተካክሏል።

ለ. በዳይሬክተርነት አገልግለው በከፍተኛ አፈጻጸም የሚያጠናቅቁ ተመራማሪዎችን በተመለከተ፤

1. በተሻሻለው መመሪያ ገፅ 10 ንኡስ አንቀጽ 3.6. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ስር 3.6.3. ሌሎች መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በኢንስቲትዩቱ ዋና መ/ቤት ወይም በማዕከላት በዳይሬክተርነት አገልግለዉ በከፍተኛ አፈፃፀም የሚያጠናቅቁ ተመራማሪዎች ካሉበት ደረጃ ወደ ሚቀጥለዉ ደረጃ ለማደግ ከሚያስፈገዉ የሕትመት ግማሹን (50%) ማሟላት ይጠበቅባቸዋል የሚለው ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማደግ ከሚያስፈልገው ህትመት ግማሹን (50%) ያሟሉና መልካም አፈጻጸማቸው ምክንያት የመጀመሪያውን የአገልግሎት ዘመን አጠናቀው ለሁለተኛ ዙር በማገልገል ላይ የሚገኙ ወይም ለሁለት ዙር አገለግለው በመልካም አፈጻጸም ያጠናቀቁ በሚለው የተተካ መሆኑን እገለጽኩ ከላይ የተዘዘረዘሩ ማሻሻዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

መለሰ ማርዮ ሰላሞ (ዶ/ር)
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፣

- ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለምክትል ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለአዝዕርትና ሆርቲካልቸር እጸዋት ብዝሀ ሕይወት ዳይረክቶሬት
- ለደንና ግጦሽ መሬት እጽዋት ዳይሬክቶሬት
- ለደቂቅ አካላት ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት
- ለእንስሳት ብዝሀ ሕይወት ዳይሬክቶሬት
- ለማዕከላትና ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት
- ለምርምር፣ ሥርዐትና ፕሮጀክት አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለስርዓተ ምህዳር ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

ኢ.ብ.ሕ.ኢ.